ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ

# መሬት ነጠቃ በኢትዮጵያ፡መልስ ለካሩቱሪ ኩባንያ

ካሩቱሪ ዓለም አቀፍ የተባለ የህንድ ኩባንያ ዋና ሥራ አስኪያጅ በቅርቡ ከብሉምበርግ ዜና ዘጋቢ ጋር ውይይት ባደረጉበት ወቅት በኢትዮጵያ በተለይም በጋምቤላ ክልል ድርጅታቸው እየነጠቀ ያለውን ለም መሬት አስመልክቶ ከጋዜጠኛው ለተጠየቀው የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል፡-

1. ከመኖሪያ ቦታው የተፈናቀለ ማንም የለም፤
2. ጋምቤላን የመረጥነው የሕዝቡ አሰፋፈር የተበታተነ በመሆኑ ልክ በረሃ የሆኑ ክልሎች ለምሳሌ በአሜሪካ የኔቫዳ ግዛት 100ኪሜ ያህል ስትሄድ ማንንም ሰው ሳታይ እንደምትሄደው ዓይነት ያለ በመሆኑ፡፡ ከዚህ ይልቅ በአማራ ክልል ሕዝብ ጥቅጥቅ ብሎ የሰፈረበትን የጣና ሐይቅ አካባቢን ብንወስድ በእርግጥ ‹‹የመሬት ነጠቃ›› ሊባል እንደሚችል ይህ የጋምቤላው ግን ከዚህ የተለየ መሆኑን፤
3. ኢትዮጵያ ለመታረስ የሚችል 80 ሚሊዮን ሄክታር መሬት እንዳላታና ከዚህ ውስጥ ግን 12 ሚሊዮኑ ብቻ በእርሻ ጥቅም ላይ እንደዋለ፤ በመሆኑም መንግሥት ከውጪ በመዋዕለ ንዋይ መልኩ ከ3 ሚሊዮን በላይ ገቢ ማድረግ እንደሚችልና ከጉዳቱ ይልቅ ጥቅሙ እንደሚያመዝን፤
4. ነዋሪዎችን መልሶ ስለማስፈር በተለይም የኢሊያ ነዋሪዎችን ወደ ሌላ ቦታ ስለመውሰድ ኩባንያው የማይፈቅደው ቢሆንም በተለይ በእርሻ መሬቶች አካባቢ ያሉቱን በሌሎች ቦታዎች የማስፈር ሥራ እየተካሄደ መሆኑን፤
5. ለኢሊያ ነዋሪዎች የወባ መከላከያ መረቦች፣ የመብራትና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች እንዲያገኙ በመደረጉ ኩባንያው ከነዋሪዎች ጋር ‹‹ፍጹም ስምምነት›› መፍጠሩ፤

በመጥቀስ ነበር መልስ የሰጡት፡፡ በእርግጥ ካሩቱሪ መሬታችንን እየነጠቀ ነው ያለው ወይስ ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት መሠረት ለማኅበረሰቡ ተገቢውን እያደረገ መሬቱን ‹‹በሊዝ በመግዛቱ›› ከውጪ የሚመጣን ኢንቨስትመንት እያጎለበተና ለአገሪቷ የውጪ ምንዛሪ ፍላጎት ላይ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ነው? ጉዳዩ እንዲህ አለመሆኑን ንቅናቄያችን ያምናል፤ ማስረጃውንም እንደሚከተለው በነጥብ እናቀርባለን፡፡

1. ከመኖሪያ ቦታው የተፈናቀለ ማንም የለም፤

በአሁኑ ጊዜ ካሩቱሪ መሬቱን ተረክቧል፡፡ ሆኖም ቦታውን የማጽዳትና ማምረት የመጀመሩ ተግባራት ገና በጅማሬ ላይ ያለ ሲሆን በርካታ ያካባቢው ነዋሪዎች ከቤታቸውና ከመሬታቸው በቅርቡ እንደሚነሱ ተነግሯቸው ይህንን ተግባራዊ የማያደርጉ ከሆነ ግን በግዳጅ ወደሰፈራ መንደር እንደሚሸጋገሩ ተነግሯቸው ነበር፡፡ *(ከጥቂት ቀናት በፊት ዋልታ*[1] *እንደዘገበው ከሆነ በጋምቤላ ክልልየመንደር ምስረታ እየተካሄ መሆኑን ገልጸ የሚደረግበትንም ዋና ዓላማ የክልሉን ነዋሪዎች ‹‹ከጎርፍ አደጋ መከላከል›› እንዲሁም ‹‹የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ፤ . . . ተበታትነው የሚኖሩ የኀብረተሰብ ክፍሎችን በመንደር በማሰባሰብ የትምህርት፣ የጤና፣ የንፁህ መጠጥ ውኃና የመንገድ ግንባታን ጨምሮ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ለማስፋት›› እንደሆነ በመናገር ‹‹በዚህ ዓመት ብቻ 15ሺ የቤተሰብ መሪዎችን በ49 መንደሮች ለማስፈር ታቅዶ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መጀመሩን›› አስታውቋል፡፡)* ይህ ሁሉ የሚያሳየው ካሩቱሪ

[1] http://amharicpage.waltainfo.com/index.php?option=com_content&task=view&id=24170&Itemid=150

መሬቱን ለመረከብ እና ተግባራዊ ሥራውን ለመጀመር የሚያስችለውን ተግባራት አገዛዙ እያመቻቸለት መሆኑን ነው፡፡

ይህ ሁኔታ እየተካሄደ ያለው በኢሊያ ብቻ ሳይሆን በባሮ (ኦፔኖ) ወንዝ አካባቢ ባሉት አቦቦ፣ ጆር፣ ዲማ፣ ጎግ እና ጎደሬ በተባሉ ወረዳዎችም ጭምር ለሚኖሩት በቅርቡ ወደሰፈራ መንደር እንደሚሄዱ ተነግሯቸዋል፡፡ ሆኖም ግን በእነዚህ መንደሮች የሚኖሩት ወገኖቻችን ቤታቸውንና አካባቢያቸውን ለቅቀው እንደማይሄዱ በመናገራቸው በአሁኑ ጊዜ የመንግሥት ወታደሮችና ሌሎች የደኅንነት ሰዎች በአካባቢው ከመቼውም በበለጠ ሁኔታ ተበራክተው መታየታቸው ለነዋሪው በግዳጅ ከአካባቢው መፈናቀል አይቀሬነት ጉልህ ማስረጃ የሚሰጥ ነው፡፡ ከሁለት ሳምንታት በፊት በአቦቦ የሚኖር አንድ ወጣት ያካባቢውን ሽማግሌዎች ቤታቸውንና መሬታቸውን ትተው የትም እንዳይሄዱ እየቀሰቀሰ ነው በሚል በመንግሥት የጥበቃ ኃይሎች በቁጥጥር ሥር ውሏል፡፡

ሌላው ከፍተኛ አወዛጋቢ የሆነው ጉዳይ ካሩቱሪ የአኙዋኮችን የቀብር ቦታን አጽድቶ ለራሱ መጠቀሚያ ማድረጉ ነው፡፡በዚህ ድርጊት አገሬው እጅግ የተቆጣ ቢሆንም ከዚህ በፊትበደረሰበት አሰቃቂ ግድያና አሁንም ካለበት ከፍተኛ ቁጥጥር ዝም ያለ ቢሆንም እንደዚህ ያለው የሕዝብ ቁጣ ወደፊት ወደየት ሊሄድ እንደሚችል ማንም ለመገመት የሚያዳግተው አይደለም፡፡ ስለሆነም ምንም እንኳን የካሩቱሪ ስራአስኪያጅ ማንም የተፈናቀለ ሰው የለም ቢሉም የአካባቢው ሰው ይሁንታ ሳይጠየቅ እንደዚህ ያለ የሰብዓዊ መብት ረገጣና የመሬት ነጠቃ



እየተካሄደ መሆኑ በግልጽ የሚታይ ነው፡፡

2. በጋምቤላ የሕዝብ ስብጥሩ የሳሳ ነው . . .

የሚለው የካሩቱሪ አባባል ሌላ ጥያቄ እንድናነሳ ይገፋፋናል፡፡ ምን ያህል የሕዝቡ አሰፋፈር የሳሳ ቢሆን ይህ የመሬት ነጠቃ በትግራይ ይካሄድ ነበር ወይ? የማይካሄድበት ምክንያቱ በርካታ እንደሆነ ለሁላችንም ግልጽ ነው፡፡ ሆኖ ግን ካሩቱሪ ሊገነዘብ የሚገባው በአሁኑ ጊዜ እየተዋዋለ የሚገኘው በሕዝብ ካልተመረጠ ሕገወጥ መንግሥት ጋር በመሆኑ ኢትዮጵያውያን በራሳቸው ጉዳይ ላይ እንዳይናገሩ አፋቸውን ሸብቦ እነርሱን ከማይወክል መንግሥት ጋር ከፍተኛ የሆነውን የአገር ጉዳይ ላይ የሚደረግን ስምምነትም ሆነ ውል በፍጹም እንደማይቀበሉት ሊታወቅ ይገባል፡፡ በተለይ ደግሞ የጋምቤላ ሕዝብ በዚህ ጉዳይ ላይ ድምጹን እንዲሰጥና ሃሳቡን እንዲናገር አለመደረጉ ልክ አንድ ሰው ወደቤታችሁ መጥቶ ‹‹እንደማየው ከሆነ በርካታ ክፍሎች ያሉት ቤት ነው ያለህና የማትጠቀምባቸውን ክፍሎች እኔ ስለምፈልጋቸው ከዛሬ ጀምሮ ወስጃቸዋለሁ›› ከማለት የማይተናነስ ነው፡፡

3. ኢትዮጵያ ለመታረስ የሚችል 80ሚሊዮን ሄክታር መሬት አላት ሆኖ 12ሚሊዮኑ ብቻ ነው በእርሻ ጥቅም ላይ የዋለው፤ የመሬቱ መሸጥ ለአገሪቷ ጥቅም ያስገኛል፤

ስለኢትዮጵያና ስለ ሕዝቦቿ ጥቅም በቅድሚያ ግድ ሊለው የሚገባው ማነው? በሕገወጥ መንገድ ሥልጣን የያዘው አገዛዝም ሆነ ሐቅን በመደበቅ ኢፍትሐዊ ተግባር የሚፈጽመው ካሩቱሪ አይደሉም፡፡ በእርግጥ ይህ ውል የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስከብር ከሆነ ለምንድርነው በድብቅ የሚካሄደው? የጋምቤላ ክልል ነዋሪዎች እንዲጠቀሙ ከሆነ ዋናው ዓላማ ለምንድነው የክልሉ ሕዝብ በስምምነቱ ውስጥ ያልተካተተውና ሃሳቡን ያልተጠየቀው? ተመሳሳይ ጥያቄ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በደቡብ ክልል፣ በአፋር፣ በኦሮሚያና አማራ ክልሎች እየተካሄደ ባለው የመሬት ነጠቃ ተግባር የክልሉና ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይጠየቅ እየተፈጸመ ያለው ለምንድነው?

ሌላው ኢትዮጵያውያን ባጠቃላይ ከዚህ የመሬት ነጠቃ ተግባር አንዳች ጥቅም እንደማያገኙ በአንክሮ የሚረዱት መሆኑ ነው፡፡ እነዚህ ሰፋፊ የእርሻ መሬቶች ለ99 ዓመት በሊዝ ሲሰጡ አሁን ያለው ትውልድ ብቻ ሳይሆን መጪው ትውልድ ጭምር በመሬቶቹ ላይ አንዳች ጥቅም እንዳያገኝ የሚከለክል ነው፡፡ የዛሬ 5 ወይም 10 ወይም 20 ዓመት የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱን አስተዳዳሪዎች በመምረጥ ራሱ ማስተዳደር በሚጀምርበትና የእርሻ ፖሊሲዎች ሕዝቡን እንደሚጠቅሙ ሆነው በሚቀረጹበት ጊዜ እንዲሁም ኢትዮጵያውያን ራሳቸው የመሬታቸው አስተዳዳሪ በሚሆኑበት ጊዜ አሁን ካሩቱሪ እየነጠቀ ያለው መሬት በኢትዮጵያውያን የሚለማ ነው የሚሆነው፡፡ ያኔ የመሬቱ ባለቤት ማን እንደሚሆን ካሩቱሪ አስቀድሞ ሊገነዘበው ይገባል፡፡ ምክንያቱም የኢትዮጵያ ሕዝብ በምጽዋት እየኖረ እንደ ካሩቱሪ ያሉ ኩባንያዎች ራሳቸውን እየጠቀሙ እና የእነአቶ መለስን ኪስ እያደለቡ ለሕዝቡ የሚጠቅም የኢንቨስትመንት ሥራ እየሠራን ነው በማለት ሕዝብን ማታለል አይችሉምና፡፡

4. ኩባንያችን የማይደግፈው ቢሆንም ነዋሪዎችን መልሶ የማስፈር ውይይት እየተካሄደ ነው፡፡

ካሩቱሪ ይህንን ይበል እንጂ በአሁኑ ጊዜ እየተካሄደ ያለው ነገር ከዚህ የተለየ ነው፡፡ የክልሉን ነዋሪዎች ‹‹ከጎርፍ አደጋ መከላከል›› እንዲሁም ‹‹የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ፤››[2] ወዘተ በሚል ምክንያት የመንግሥት ባለሥልጣናት በተገኙበት መልሶ የማስፈሩ ተግባር እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ምንም እንኳን ይህንን ዓይነት ምክንያት ቢሰጥም ከበስተጀርባው ያለው ምክንያት ግን እነካሩቱሪ ሥራቸውን በቶሎ ለመጀመር እንዲችሉ አካባቢውን የማጽዳት ተግባር ነው፡፡በዚህ




የማፈናቀል ተግባር እየተጎዱ ያሉት የኢሊያ ነዋሪዎች ብቻ ሳይሆኑ የተወሰኑ የኑዌርና የመጀንጂር ሕዝቦች ከሚኖሩበት ቦታ በማስነሳት ረገድ ቀጣዩ ዒላማ እንደሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ካሩቱሪ እንዳለው ጉዳዩን ‹‹አናውቅም፤ አንደግፍም›› ቢልም አንድ የማይዘነጋ

---

[2] http://amharicpage.waltainfo.com/index.php?option=com_content&task=view&id=24170&Itemid=150

ሐቅ ግን ምንም እንኳን የመሬት ነጠቃው ጉዳይ መንግሥት ሆን ብሎ ያቀደው ተግባር ቢሆንም ይህ ኩባንያ ወደዚያ ባይመጣ ኖሮ እነዚህ ሕዝቦች አይፈናቀሉም ነበር፡፡ የሆነው ሆኖ የአንድ ኩባንያን ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል እነዚህ ሕዝቦች ያለፈቃዳቸው ከመኖሪያቸው መነሳታቸው ፈጽሞ ቸል የሚባል አይደለም፡፡ ካሩቱሪም ‹ድርጊቱን አንደግፍም› ብቻ በማለት እንደጲላጦስ ‹‹ከደሙ ነጻ ነን›› ማለት አይችልም፡፡

5. የኢሊያ ነዋሪዎች የወባ መከላከያ መረቦች፣ የመብራትና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች እያገኙ ነው፡፡ በመሠረቱ ይህ ሃሰት ነው፡፡ ለንቅናቄያችን ከአካባቢው የሚመጡ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ባሁኑ ጊዜ የአካባቢው ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ ከበፊቱ ፍጹም ያልተለየና የተባሉትም ጥቅማጥቅሞች ፈጽሞ እንደሌሉ ነው፡፡ የመብራት አገልግሎት ባካባቢው የለም፣ የወባ መረቦችም የደረሰው የለም፡፡ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ህዳር 10፣ 2003 ዓም ድረስ ብቸኛው የውሃ ጉድጓድ ያለው በካሩቱሪ ቅጥር ግቢ ውስጥ ሲሆን የኩባንያው ሰዎች የአካባቢውን ነዋሪዎች ውሃ ሲፈልጉ ወደኩባንያው እየመጡ መጠቀም ትችላላችሁ ብለዋቸዋል፡፡ ሆኖም ግን በካሩቱሪና በአካባቢው ነዋሪዎች መካከል ‹‹ፍጹም ስምምነት›› እየተፈጠረ ከሆነ የውሃው ጉድጓድና ሌሎች ጠቃሚ ነገሮች ከኩባንያው ቅጥር ጊቢ ውጪ ያልተደረጉት ለምንድነው? ነዋሪዎች ከቀያቸው እየተፈናቀሉ፣ የመቃብር ቦታ ‹‹ለልማት እየዋለ››፣ ነዋሪዎች ከአካባቢያቸው መሄድ አንፈልግም እያሉ በግድ እያፈናቀሉ፣ ወዘተ ኢፍትሃዊ ተግባራት እየተካሄዱ ለመሆኑ ‹‹ፍጹም ስምምነት›› ማለት ምንድነው?ይህ የአገዛዙ ፕሮፓጋንዳ ሰዎች የሚደሰኩሩት በካሩቱሪ መደገሙ አሳፋሪ ነው፡፡

‹‹መሬት ነጠቃ›› ቃሉ በግልጽ እንደሚጠቁመው የራስ ያልሆነን ነገር አለአግባብ ወይም በኃይል ለራስ ማድረግ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ተግባር በተለይ የሚደፈጸመው መብታቸው ፍጹም በተረገጠና ራሳቸውን መከላከል በማይችሉ ለአደጋ በተጋለጡ ሕዝቦች ላይ መሆኑ ድርጊቱ ፈጽሞ ኢሰብዓዊ ያደርገዋል፡፡ እንደ ካሩቱሪ ያሉ ኩባንያዎች ይህንን ማድረጋቸው በእጅአዙር ቅኝ አገዛዝ እየተሳተፉ መሆናቸውን እነርሱም አያጡትም፡፡ አሁን በጋምቤላና ሌሎች ክልሎች የሚካሄደው የመሬት ነጠቃ በኒውዴልሂ ህንድ፣ በኦክስፎርድ እንግሊዝ፣ በሳስካቱን ካናዳ፣ በኖርዝ ዳኮታ አሜሪካ፣ ወዘተ እንኳን ሊፈጸም አይደለም ሊታሰብም አይችልም፡፡ የትም ተፈጸመ የት ግን ልናስተውለው የሚገባው ዓቢይ ነገር ስህተት ያው ስህተት ነው፡፡ አንድ የጋምቤላ ሰው ወደ ሕንድ ሄዶ የአካባቢውን ሰዎች ፈቃድ ሳይጠይቅ የፈለገውን ለም መሬት ቢወስድ ህንዶች መልሳቸው ምንይሆን? በየትኛውም መልኩ እንየው ይህ አውሮጳውያን አፍሪካን ለመቀራመት በበርሊን ካደረጉት ስምምነት ፈጽሞ የሚለይ አይደለም፡፡

ባለፉት በርካታ ዓመታት የጋምቤላ ክልል ነዋሪ ከፍተኛ በሆነ ጭቆናና የመብት ረገጣ ሥር ይገኛል፡፡ በተለይ የዛሬ ሰባት ዓመት ወደፊት ሊደረጉ ለታሰቡ የነዳጅ ፍለጋም ሆነ አሁን እየተገበረ ያለው የመሬት ነጠቃ እንቅፋት ይሆናሉ ያላቸውን የአገር ሽማግሌዎች እንዲሁም ሌሎች በሺዎች የሚቆጠሩ ነዋሪዎችን በማስወገድ ህወሃት/ኢህአዴግ በአኙዋክ ሕዝብ ላይ ያደረሰው የዘር ማጥፋትና ጭፍጨፋ ሃዘኑ ገና ያላለቀ፤ ደሙም ገና ያልደረቀ ነው፡፡ አሁንም ሊከናወን የታሰበውን ማንም አያውቅም፤ ሆኖም ግን ካሩቱሪ ከአካባቢው ነዋሪ ጋር ‹‹ፍጹም ስምምነት›› እንዲኖረው ካሰበ አሁን እየወሰደ ባለው አቋሙ ላይ እንደገና ሊያስብበት ይገባል፡፡

**ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ**

**************************************************************************************************************

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ ዋና ዳይሬክተሩን ለአቶ ኦባንግ ሜቶ (obang@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡፡*

